## የተሰወረው ድርሳነ - ወያኔ

ታሪኩ አባዳማ

ባለፈው አፕሪል መጀመሪያ ግድም ዋሽንግተን ዲሲ ከሚገኘው የናሽናል ጂኦግራፊ ሙዚየም ለሕዝብ እይታ ቀርቦ የነበረው “The Lost Gospel of Judas” ጉዳይ እስካሁን ይከነክነኛል። የጎብኚውን ቀልብ እጅግ አድርጎ ከሳበው ነገር መጽሐፉ ከ1770 ዓመታት በሁዋላ (እአአ) በ1970ወቹ ዓመታት ግብፅ ውስጥ የወሮበሎች ቡድን (በጉብኝቱ ወቅት በአሰተናባሪ ምሁራን እንደተነገረን) ባደረገው ቁፋሮ ከተቀበረበት መውጣቱ ብሎም በተለያዩ ደላሎች ቅብብሎሽ አልፎ መጨረሻ ከናሽናል ጂኦግራፊ ሙዝየም መድረሱ ነበር። ተቋሙ ብዙ ገንዘብ አፍሶ ነው በመጨረሻ መጽሐፉን እጁ ሊያስገባ የበቃው። ድንቅ ታሪክ ነው።

The Lost Gospel of Judas ተገቢ ጥገና ከተደረገለት ወዲህ በጥንቃቄ እየተመረመረ ሲሆን በቅድሚያ እውነትም ይሁዳ ጽፎት እንደሆን በማያሻማ ሁኔታ መረጋገጡ ተገልፁዋል። ይሁዳ ፣ ጌታ እየሱስን በ30 ዲናር የሸጠ ፤ የጌታን ፍቅር እና አደራ የረገጠ ፣ ጌታ እንዲንገላታ እና እንዲገደል አሳልፎ ለጠላቶቹ የጠቆመ ከሀዲ ነው ተብሎ በክርስትና ተከታዮች ዘንድ ከትውልድ ትውልድ ሲረገም የቆየ የቀድሞ ደቀ-መዝሙር መሆኑ ነው። በቁፋሮ የተገኘው ይህ መጽሐፍ በርካታ የሆኑ አዳዲስ ጉዳዮች እንዳዘለ ምሁራኑ ያስገነዝባሉ። ዝርዝሩን እናንተው አንባቢዎች በቀላሉ የናሽናል ጂኦግራፊን በመጎብኘት ወይንም ድረ-ገፁን በመፈተሽ ልታገኙት እንደምትችሉ በማመን በዚያ የተነሳ የሆነ ትውስታ ወደ ጫረብኝ ጉዳይ እና ለዚህ ጽሁፌ መነሻ ወደሆነው ሌላ “የጠፋ መጽሐፍ” ጉዳይ ልውሰዳችሁ።

ዛሬ ረፋዱ ላይ የ“ethiomedia”ን ድረ-ገጽ ሰከፍት ፣ “እባካችሁ ፣ መለስ ዜናዊ ‘የኤርትራ ትግል ከየት ወደየት’ ብሎ ከዚህ ቀድም የፃፈውን ድርሳን አፈላልጉን” የሚል ማስታወቂያ ማየቴ ከወር በፊት ያደረኩትን ጉብኝት ፋይዳ ዘራበት። የመለስ ጽሑፍማ ፀሐይ የሞቀው ፣ የወያኔ በኩር ካድሬዎች (እስከ ባድመ ጦርነት ድረስ) ሲያደርጉት በነበረው ቅስቀሳ ሁሉ እንደ ንድፈ-ሃሳብ ምንጭ አድርገው በኩራት ሲጠቃቅሱት የነበረ መሆኑን የምንስተው አይመስለኝም።

ታዲያ ከባድመ ጦርነት በሁዋላ የመለስን ጽሑፍ ምን በላው? ሚሌንየምን አከብራለሁ ካለ ወዲህ ደግሞ መጽሐፉ ከቶውንም ተጽፎ እንዳልነበር ያህል ዱካው ጠፍቷል። እንደ The Lost Gospel of Judas ተቀብሮ ይሆን እንዴ? በይሁዳ ዘመን የጽሑፍ ማባዣ ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ ያው አንዱ ቅጂ ተቀብሮ ፣ ዘመን በዘመን ተተክቶ በቁፋሮ ተገኝቷል። እውነትን ምን ዝቅ አድርገው ቢቀብሯት ይፋ መውጣቷ እንደማይቀር አንድ ተስፋ የሚሰጥ ግኝት ነው ማለት ይቻላል።

መለስ ብዙ ዝባዝንኬ ጽፏል። ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ስለ አልባንያ የነጠረ ሶሻሊዝም ፣ ስለ እስታሊን ብርዝ ክልስ የሌለው ኮምኒዝም ፣ ስለ ሸአቢያ ዲሞክራሲያዊ ድርጅትነት ፣ ስለ ትግራይ መገንጠል እና የራስ መንግስት መመስረት ፣ ስለ መቶ ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ …ወዘተ ። ታዲያ ይህን ሁሉ ጽሁፍ በወግ ጠብቆ የማቆየት ግንባር ቀደም ሀላፊነት ያለበት የመለስ ልዩ የህወሀት ቡድን ቀብሩን አቀላጥፎት እንዳይሆን ያሰጋል። ተቀብሮ የሚቀር ነገር እንደሌለ ደግሞ ከይሁዳ መጽሐፍ ይማራሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

አሁን በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሚሌኒየምን ለማሰብ ፣ በሚሌንየም መንፈስ በዘመኑ የተነሱ ከሀዲዎችን ለማሳፈር እየተዘጋጀ ያለበት ታሪካዊ ወቅት ነው። ኢትዮጵያውያን  የከሀዲው ጽሁፍ ተቀብሮ ገና የቁፋሮ አሰሳ መሂድ አንፈልግም። የከሀዲውን ጽሁፍ በሙዚየም ሳይሆን በአደባባይ አውጥተን መመርመር እና ለሕዝባችን ይበልጥ ግንዛቤ ማስጨበጫ ዋቢ አድርገን ልንገለገልበት ይገባል። አትዮሚዲያ ቀንቶት የከሀዲውን ሰነድ እንደሚያገኝ ተስፋ አደርጋለሁ፣ ታዲያ ያገኛችሁትን ብታቋድሱን ሸጋ ነው።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com